# አውራ አልባ ንቦች
## (ክፍል ሁለት)

ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሣ

እንደዚህ ሆነና፥ ከዝንቦቹ ፍጅት
በታላቅ ታምራት ያመለጡት ንቦች፥
ጥቂት ሲያገግሙ ተሰበሰቡና፥
"ተሳስተን ነበር በመሰሪ ዝንቦች፥
"በሉ ልብ እንግዛ፥እንሂድ ወደ አውራችን፤
"ይቅር ተባብለን እንግባ ቀፎአችን"፥ ቢሉ ጥቂት ንቦች፥
አንድ ንብ ጠየቀ-"ኧረ ለመሆኑ በአውራው ያመጽነው፥
"ክቡር ንቦች ሳለን ሆነን እንደዝንቦች፥
"በአብላጫው ንቦች ራሳችን መርጠነው፥ እኛው ያከበርነው
"ይህን ትልቅ አውራ አንሻህም ካልነው፥ በሥነሥርአቱ
"በክብር ማሰናበት፥ መቻሉን ረስተን ነው በሱ ላይ ያበርነው?"

ሁለተኛው አለ "ቆይማ፥ ነገሩ አይደለም እንደሱ፥
"ቆስቋሾቹ ዝምቦች ቢሆኑም መነሾው፥
"እኛው ውስጥ ነበር የተጠነሰሰው
"ጠቡ እንዲፈላ ያደረገው እርሾው-
"አውራው ጨቁኖናል
"በቀጭን ትዕዛዙ፤
"እኛን ሳያማክር ሁሉን በማዘዙ፥
"ቀፎው ተበጥብጧል
"ቢበዛ መዘዙ::
"አበባ ላበባ ተንከራተን ውለን፥
"ቀስመን ጣፋጭ አውላ በተራ በተራ፥
"ማሩን እየቀመምን በጋራ እየጋገርን፥
"ስንከምር እንጀራ፥
"ትዕዛዝ መስጠት'ንጂ
"አይተባበርም ከቶም ከኛ ጋራ!
"እንደጌታ አውራ'ንጂ
"በምንም አይሆንም እንደባልንጀራ፤
"ለዚህ ነው ያመጽን
"ምንም ቁስቆሳውም በዝምቦች ቢሠራ::"

ይህን አንድ ንብ ቢል ተነሳና ሌላው፥
"ምኑን አውራ ሆነ ካላዘዘ አውራ?"
በማለት አወራ፥ "መካሪ ከበዛ፥
"ሐሳብ ተበታትኖ ሥራም አይሠራ!
"ሺ ቢያጭኽ አንድ ያገባሽ፥
"ሺ ቢመክር አንድ ይመራ፥
"ቀድሞም ታይቶ አያውቅም
"አእላፍ ንብ ሲመራ፤
"ጥንትም ዛሬም አለው
"አእላፍ ንብ አንድ አውራ፥
"ሁላችን ከመራን

“ታላቅ ቀውስ ተፈጥሮ ያመጣል መከራ!
“አውራው አጠፋ ካልን÷
“በማፈንገጥ ፈንታ ይገባናል መምከር÷
“መክሮም ማሳመን ነው፤
“እስከምንስማማም ተግቶ መከራከር፡፡”

“የተርቦች ጥፋት ነው!”
አለ ሶስተኛው ንብ
“የተርብ ጥፋት ለምን
“ይሳበባል በዝንብ?
“ተርብ ሆነው ሳለ÷ ልክ እንደኛው ሁሉ
“የሚሉ ንቦች ነን÷
“አውራውን ከበዉት÷ ያንን ምስኪን አውራ
“አሳቱት አጓጉል ሆነው አምባገነን፡፡
“ማሩን እየዛቁ እየበሉ አደራ÷
“ተርቦች ቦጠቦጡን÷ ደሞም በጠበጡን÷
“ችሎታ-ቢስ ናቸው፤
“ወይም አያሠሩን ወይ አይሠሩ ሥራ
“ንቦች መስለው ቀርበው
“እንቅፋት ሆኑብን÷ አሳዩን መከራ፡፡
“አውራውን ገንጥለን ከተርቦቹ መሃል÷
“ወደኛ ወስደነው÷
“ከነሱ አትርፈነው÷
“በሉ እንረባረብ እሱን እናድነው÷
“ይህን ለመፈጸም የኛ ግዴታ ነው፡፡”

“ተርብ÷ተርብ አትበሉ÷
አለ ዓራተኛው “ሁላችን ንቦች ነን!”
“እንዲህ መከፋፈል ይጠቅማል ዝምቦችን÷
“መቻቻል ብቻ ነው እኛን የሚያድነን!”

ይህን ተባብለው አሉትም አውራውን-
“ከጦርነት ሠላም÷ከጥል እርቅ ብለን÷
“ይኸው የተረፍነው ተመልሰን መጣን
“ለቀፎው አይበጅም መጥፋቱ ኮብለን፡፡”

አውራው ተደስቶ÷ “መልካም አርጋችኋል÷
አላቸው ለሁሉም “ከምንበታተን መሻታችሁ ፍቅር÷
“ሳጠፋ ምከሩኝ÷ ከበደልኩ ውቀሱኝ፤
ስለፍቅር በስመአብ ይቅር፡፡
እንምረጥ ብትሉም ከኔ ሌላ አውራ÷
አድርጉት በወጉ÷ አይሁን ሥርአት አልባ÷
በክብር እንለያይ ሕግ ደምብ ጠብቀን÷
ማሩን እንዳይዘርፈው ያእላፍ ዝምብ ሌባ፡፡

እንደዚህ ሆነና
ባውራና ንብ መሃል እርቅ ወረደና÷
ጻግም ፍቅር ጸና!

እየተባበሩ ማር መሥራት ጀመሩ፤
ተጠናከሩና ህይወት ሆነ ደህና፤
ግለኞች ከመሆን ኃርዮሽን መርጠው፥
ለሁሉም በጎነት ጀመሩ እንደገና-
እንዳማረባቸው መራመድ ወደፊት፥
ዝንቦች አቃታቸው ፍቅርን ሊያፈርሱ፥
ራሳቸው በነኑ በንቦች ህብረት ፊት፤
ንቦች ተባበሩ በፍቅር ጠንክረው፥
ተምዘግዝገው ሄዱ ያለዝንቦች ግፊት፡፡

እ ኤ አ መስከረም 20 ቀን 2007